# የአንድነት የአዳማ ስብሰባ በተቃውሞ ተቋረጠ

## የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕ/ት ዶ/ር ነጋሶ ድብደባ ተፈፀመባቸው

በውብሸት ታዬ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በናዝሬት (አዳማ) ከተማ ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ከትናንት በስቲያ ረፋድ ላይ ያደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ አዳራሹ ውስጥ በተገኙ የአካባቢው ተወላጆች ተቃውሞ ተቋረጠ፡፡

የአዳማ ከተማ መስተዳድር ከንቲባ ጽ/ቤት ለሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ፓርቲው ሕጋዊ ስብሰባ ለማካሄድ የሚያስችለውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ መላኩን ከጽ/ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመለከተ ሲሆን አንድነት በትናንትናው እለት «የፖለቲካ ምህዳሩ በተግባር ሲዳፈን» በሚል ርዕስ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ሁነቱን፣ «የኢሕአዴግ የፓለቲካ ምህዳሩን የማጥበብና ቀስ በቀስ የማዳፈን ፍላጐት» ሲል አጥብቆ ተቃውሞታል፡፡

በማዘጋጃ ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ስብሰባው ተጀምሮ የመግቢያ ንግግር ከተደረገ በኋላ «አካሄድ» የሚል ቁጣ የተቀላቀለበት ጥያቄ ከተሰብሳቢዎቹ በተቃውሞ ቀርቧል፡፡ «የአካሄድ  ችግር» በማለት ተቃውሞውን የቀሰቀሱት ግለሰቦች ያቀረቧቸው የማስተካከያ ጥያቄዎች፣ «ክልሉ የኦሮሚያ ክልል ሆኖ እያለ እንዲሁም የቅስቀሳ ወረቀቶች ያሰራጫችሁት በኦሮምኛ ቋንቋ ሲሆን አሁን ስብሰባው እየተካሄደ ያለው ግን በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ በአስቸኳይ አቁሙ!»፣ «በኦሮሞ ባሕል ስብሰባ የሚጀመረው በአገር ሽማግሌዎች ምርቃት ቢሆንም ይህን ያልፈፀማችሁት በንቀት ነው!» የሚሉ ነበሩ፡፡ ከዚህ በኋላ አዳራሹ በከፍተኛ ጩኸት፣ ጭብጨባና ፉጨት በመናጡ ስብሰባው ሊቀጥል አልቻለም፡፡

የተፈጠረውን ተቃውሞ ለማረጋጋት የሞከሩ የፓርቲው ሁለት አባላት የተደበደቡ ሲሆን በክብር እንግድነት በተገኙት ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ እና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ላይ መጠነኛ እንግልት ደርሶ ከአዳራሹ ወጥተዋል፡፡ በክብር እንግድነት ከተገኙት የፓለቲካ ሰዎች አንዱ የሆኑት አቶ ስዬ አብርሃ፣ በአንፃራዊ ሁኔታ ተቃውሞ ካስነሱት ተሰብሳቢዎች ወከባ ሳይደርስባቸው ይልቁንም መንገድ እየተለቀቀላቸው የወጡ ሲሆን ይህም በአንዳንዶች ላይ ግርምትን ያጫረ ክስተት ሆኖ አልፏል፡፡

በተለይ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን «ለነፍጠኞች አሳልፈው የሰጡን» የሚል ዘለፋና መጠነኛ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት እንደነበሩ ይታወሳል፡፡